# በከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር

## የኮንስትራክሽን አማካሪዎች የአሰራር ረቂቅ መመሪያ ቁጥር ፰፻፹፩/፪ሺ፲፬

## Construction Consultants Procedure Directive Draft No. 881/2022

መጋቢት 2014 ዓ.ም

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

| የኮንስትራክሽን አማካሪዎች የአሰራር ረቂቅ መመሪያ ቁጥር ፰፻፹፩/፪ሺ፲፬ | **Construction Consultants Procedure Directive Draft No. 881/2022** |
|---|---|
| በኮንስትራክሽን ኢንደስትሪ ውስጥ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ በጀት እና የጥራት ደረጃ መጠናቀቅ ባለመቻላቸው ችግሮችን ለመቅረፍ የአማካሪ ሚና ከፍተኛ በመሆኑ፣ ኢንዱስትሪው የሚመራበትን የአሰራር ስረዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፣ | In the construction industry, the role of consultant is crucial to solving problems due to the inability to budget and quality projects on time, and the need to establish an industry-leading system. |
| አማካሪዎች በገቡት ውል መሠረት ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው በጅምር የቀሩ እና ተጠናቀው ርክክብ ያልተፈጸመባቸው በመበራከታቸው፣ በርካታ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች በጥቂት አማካሪዎች ብቻ በመያዛቸው ተወዳዳሪነትና አማራጭ እንዳይኖር በማድረግ በኢኮኖሚው ላይ የሚፈጥረውን አሉታዊ ተጽእኖ ለመከላከል የአማካሪ የአሰራር መመሪያ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣ | Due to the large number of consultants who failed to fulfill their obligations under the contract, many construction projects were held by only a few consultants and it was necessary to develop a consultative policy to prevent negative impact on the economy. |
| የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ጤናማ እድገቶች የሚጎዱ መልካም ያልሆኑ ገፅታዎችን፣ ለመቀየር በዘርፉ የሚሳተፉ አማካሪዎች የሚመሩበት የቁጥጥርና ተጠያቂነት ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣ | The need to establish a regulatory and accountability system led by consultants involved in the sector to change the negative aspects that affect the healthy growth of the construction industry. |
| ኃላፊነታቸውን በትክክል በማይወጡትና በህዝብ ሀብት ላይ በሚያደርሱት ጉዳትና ኪሳራ ተጠያቂ የሚያደርግ መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የከተማና መሠረተ-ልማት ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 19(4) በህግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡ | The Ministry of Urban and Infrastructure has issued this directive in accordance with the authority vested in it by Article 19 (4) of Proclamation No. 1263/2014, as it is necessary to issue a directive to hold those responsible for their misconduct and damage to public resources accountable. |

**<u>ክፍል አንድ</u>**

**<u>ጠቅላላ ድንጋጌ</u>**

1. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ መመሪያ “የኮንስትራክሽን አማካሪዎች የአሰራር መመሪያ ቁጥር ፰፻፹፩/፪ሺ፲፬” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **<u>ትርጓሜ</u>**

በዚህ መመሪያ ውስጥ ፡-

1) “ኮንስትራክሽን” ማለት ከመሬት በታችና በላይ የሚከናወኑ ህንጻን እና ሌሎች የምህንድስና መሠረተ ልማትን ጨምሮ በቋሚ ንብረቶች ላይ የግንባታ የዕቃዎች እና አገልግሎቶች ጥምር የሆነ የልማት፣ የማስፋፋት፣ የመገጣጠም፣ የጥገና፣ የዕድሳት፣ የማሻሻል እና የቁፋሮ ሥራዎችን የሚያካትት ተግባር ነው፡፡
2) “የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት” ማለት በመንግስት፣መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች፣ በግሉ ዘርፍ እንዲሁም በመንግስትና በግሉ ዘርፍ ጥምረት የሚከናወኑ ማናቸውም ከኮንስትራክሽን ጋር ተያያዥ የሆኑ የቅድመ ዲዛይን፣ የዲዛይን፣ የግንባታ፣ የድህረ-ግንባታ ስራዎችና አገልግሎቶች በተናጠል ወይም በጋራ ማከናወኛ ማዕቀፍ ነው፡፡
3) “አማካሪ” ማለት ሕጋዊ ሥልጣን በተሰጠው አካል ተመዝግቦ በኮንስትራክሽን እና በከተማ ፕላን ዘርፎች ላይ የአማካሪነት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰጠው ድርጅት ነው፡፡
4) “የሥራ ተቋራጭ” ማለት ሕጋዊ ሥልጣን በተሰጠው አካል ተመዝግቦ በተለያዩ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ዘርፎች ላይ የሥራ ተቋራጭነት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰጠው ድርጅት ነው፡፡
5) “የዲዛይን ባለሙያ” ማለት ሕጋዊ ሥልጣን በተሰጠው አካል ተመዝግቦ የኮንስትራክሽን ዲዛይን ለመስራት የምዝገባ ምስክር ወረቀት የተሰጠው ባለሙያ ነው፡፡

**<u>Part One</u>**

**<u>General Decree</u>**

1. **<u>Short title</u>**

This directive can be referred to as the "Construction Consultants Procedure Directive No. 881/2014".

2. **<u>Definition</u>**

In this directive፡-

1) "Construction" is a combination of construction, expansion, assembly, maintenance, renovation, and excavation work on fixed assets, including underground and above-ground construction.
2) "Construction project" means a separate or joint venture of any pre-design, design, construction, post-construction work and services related to construction by any public, non-governmental, private or public-private partnership.
3) "Consultant" means an organization registered with a legal authority and certified as a consultant in the construction and urban planning sectors.
4) "Contractor" means an organization registered with a legal authority and certified as a contractor in various sectors of the construction industry.
5) "Designer" means a professional who is registered with a designated authority to perform construction design.

6) “የግንባታ ቁጥጥር ባለሙያ” ማለት ሕጋዊ ሥልጣን በተሰጠው አካል ተመዝግቦ የኮንስትራክሽን ቁጥጥር ለማከናወን የምዝገባ ምስክር ወረቀት የተሰጠው ባለሙያ ነው፡፡

7) “አሠሪ“ ማለት ማንኛውንም የግንባታ ፕሮጀክት አፈጻጸም በባለቤትነት የሚከታተልና የሚያስፈጽም ወይም ባለቤት ሲሆን ከአማካሪ ድርጅት ወይም ከሥራ ተቋራጭ ጋር ውል ገብቶ የሚያሰራ አካል ነው፣

8) “ብክነት” ማለት አማካሪው መፈጸም የሚጠበቅበትን ግዴታ ባለመወጣቱ ከጊዜ፣ ከበጀት፣ እና ከጥራት ጋር ተያይዞ የሚፈጠር ብክነት ወይም ኪሳራ ነው፡፡

9) “ቅድመ ዲዛይን” ማለት ዲዛይን ከመሰራቱ በፊት የፕሮጀክት አዋጪነት፣የመስክ ምልከታ ጥናትንና፣ የቅየሳ ሥራን ያካትታል፡፡

10) “የኮንስትራክሽን ዲዛይን አገልግሎት” ማለት የሕንጻ፣ የመንገድ እና ሌሎች የመሠረተ-ልማት ዲዛይን አገልግሎቶች አካቶ የሚይዝ ነው፡፡

11) “የኮንስትራክሽን ሥራዎች ቁጥጥር” ማለት ማንኛውም ኮንስትራክሽን በሚከናወንበት ጊዜ በግንባታ ተቆጣጣሪ አማካሪ የሚደረግ የኮንስትራክሽን ቁጥጥር ሥራ ማለት ነው፡፡

12) “የኮንስትራክሽን ሥራዎች የውል አስተዳደር” ማለት የውል አፈጻጸምን መከታተል፣ ውልን ተፈጻሚ ማድረግ እና ውልን ማጠናቀቅ ነው፡፡

13) “ሚኒስቴር” ማለት የከተማና መሠረተ-ልማት ሚኒስቴር ነው፡፡

14) “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ማንኛውም አካል ነው፡፡

15) በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

6) "Construction Supervisor" means an expert registered with a legal authority to carry out construction inspection.

7) "Employer" means the person who supervises and executes the construction of any construction project and is the person who enters into a contract with a consulting company or contractor.

8) “Waste” means a waste or loss of time, budget, and quality that the consultant has not fulfilled.

9) "Pre-design" includes project feasibility, field observation, and design prior to design.

10) "Construction Design Service" means building, road and other infrastructure design services

11) "Supervision of construction works" means construction supervision work carried out by a construction supervisor during any construction.

12) "Construction works Contract Management" means monitoring the execution of a contract, enforcing a contract, and concluding a contract.

13) "Ministry" means the Ministry of Urban and Infrastructure.

14) "Person" means any person who has been granted a natural or legal right.

15) The gender description in this guide also includes the female gender.

3. **<u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>**

1) ይህ መመሪያ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡-

ሀ/.በማንኛውም በፌደራል መንግስት፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ በፌደራልና በክልል መንግስታት በጋራ በጀት በሚገነቡ ወይም በመንግስትና በግል ትብብር በሚሰሩ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች በአማካሪነት ሥራ ላይ በሚሰማሩ አማካሪዎች ላይ፣

ለ/.በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የፌደራል መንግስት ድጋፍ ያላቸው የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ላይ፤

ሐ/.ከመንግስት የንግድና የልማት ባንኮች በሚገኙ ብድሮች በሚገነቡ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ላይ፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው ቢኖርም በሚከተሉት ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፣

ሀ/.መመሪያው በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የማማከር አገልግሎት ውል በተፈጸመባቸው የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ላይ፣

ለ/በሌሎች ሕጎች እና ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለምዓቀፍ ሕጎች ከለላ የተሰጣቸው የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ላይ፣

ሐ/ለብሔራዊ ደሕንነት፣ ሐገር መከላከያና እንዲሁም አስቸኳይ ሠው ሠራሽና የተፈጥሮ አደጋን ለመከላከል በሚተገበሩ ፕሮጀክቶች ላይ፣

4. **<u>አላማ</u>**

ይህ የኮንስትራክሽን አማካሪዎች የአሰራር መመሪያ የሚከተሉት አላማዎች ይኖሩታል፡፡

1) አማካሪዎች የኢትዮጵያን የኮንስትራክሽን

3. **<u>Scope of application</u>**

1) This directive shall apply to the following:-

a) Consulting with consultants engaged in any joint venture between the Federal Government, public enterprises, the Federal and State Governments or on public and private construction projects

b) on construction projects directly or indirectly supported by the Federal Government

c) Construction projects to be built on loans from government commercial and development banks

2) Notwithstanding the provisions of sub-article 1 of this Article, the following shall not apply;

a) Before the directive is implemented Consultation service On construction projects

b) Construction projects protected by other laws and international law adopted by Ethiopia

c) on projects for national security, national defense and emergency man-made and natural disasters.

4. **<u>Objective</u>**

This Construction Consultation Guide has the following objectives.

1) Enabling consultants fallow with Ethiopian construction laws, codes and

ህጎች፣ ኮዶችና ስታንዳርዶች ተከትለው እንዲሰሩ ማድረግ፤

2) በተገባው ውል መሠረት አማካሪው የተቀበላቸውን ኃላፊነቱንና ግዴታውን ጠብቆ የፕሮጀክቱን ታሳቢ ጥቅምና ፍላጎት ማስጠበቅ፣

3) ተጠያቂነትን ማስፈን፤

4) ሙያዊ ሥነ-ምግባር የተላበሰና ሕግን ያከበረ የኮንስትራክሽን አማካሪዎች መፍጠር፣

5) በግንባታ ወቅት የዲዛይን ለውጥ ሲኖር ሥራ ተቋራጩ ለአሰሪው በማሳወቅ አሰሪው ዲዛይኑን ያዘጋጀውን አማካሪ በማሳወቅ ዲዛይኑን እንዲለውጥ ማድረግ እና ግንባታው በተመደበለት በጀት፤ጊዜ እና ጥራት እንዲጠናቀቅ ማስቻል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የቅድመ ዲዛይን፣ የዲዛይን ሥራዎች፣ የግንባታ ቁጥጥር እና የኮንትራት አስተዳደር አማካሪ

### 5. ስለቅድመ ዲዛይን ሥራ

1) የቅድመ ዲዛይን አማካሪ የሚያዘጋጀው የፕሮጀክት አዋጭነት ጥናት፣ የቅየሳ ሥራ እና የአካባቢውን ነባራዊ ሁኔታ በትክክልና በዝርዝር የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡

2) ለተፈለገው ግንባታ አይነት የዋጋ እና የበጀት ጥናት መካሄዱን እንዲሁም በቂ የሆነ ቦታ መኖሩን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

### 6. የዲዛይን ዝግጅት አጠቃላይ ቅድመ ሁኔታዎች

አንድ አማካሪ ዲዛይን በሚያዘጋጅበት ጊዜ

standards

2) Preserve the potential benefits and needs of the project in accordance with the obligations received by the consultant in accordance with the contract.

3) Ensuring accountability

4) Creating professional ethics and law enforcement consultants

5) Notify the contractor of any design changes during construction, notify the employer of the design consultant, and allow the construction to be completed within the allotted budget, time and quality.

## Part Two

## Pre-Design, Design Works, Construction Supervision and Contract Management Consultant

### 5. Pre-design work

1) The project feasibility study, survey work and the environmental assessment should be prepared by the pre-design consultant.

2) A cost and budget study should be conducted for the type of construction required and adequate space should be provided.

### 6. General requirements for design preparation

The general requirements listed when

| | |
|---|---|
| የተዘረዘሩትን አጠቃላይ ቅድመ ሁኔታዎች መከተል ይኖርበታል፡- | designing a consultant Must follow: |
| 1) የሕንጻ፣ የመንገድ፣ የፍሳሽ፣ የከተማ ቅርጽና አውድ፣ የአረንጓዴ ስፍራ ማስዋብ፣ የድልድይ፣ እና ሌሎች ተያያዥ የመሰረተ-ልማት ዲዛይኖችን በቅንጅት ለማጣጣም ጥናት ማድረግ፤ | 1) Conduct survey study to integrate the design of buildings, roads, sewers, urban landscapes, bridges, and other related infrastructure designs |
| 2) የሚሠራው ዲዛይን ከሃገሪቱና ከአካባቢው ነባራዊ ሁኔታ ጋር አብሮ እንዲሄድ ማድረግ፤ | 2) Make the design in line with the realities of the country and the location |
| 3) እንደፕሮጀክት ዓይነቱ ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልጉ የሙያ መስኮችን ያካተቱ እርስ በእርሳቸው የተጣጣሙ ልዩ ልዩ ዲዛይኖችን መሥራት፣ | 3) Develop a variety of tailored designs that include the professional fields required for the project, depending on the type of project |
| 4) የዲዛይን ህጎችን፣ ኮዶችንና ስታንዳርዶችን እንዲሁም የከተማውን ፕላን መከተል፣ | 4) Follow design rules, codes and standards as well as city planning |
| 5) በአሰሪውና በተገልጋዩ ፍላጎት መሰረት ግንባታው በተመጣጣኝ ወጪ እንዲካሄድ የሚያስችል ዲዛይን ማዘጋጀት፤ | 5) Prepare a design that will allow the construction to be carried out cost efficient according to the needs of the employer and the customer |
| 6) ዲዛይን የሚያዘጋጀው አማካሪ በአገር ውስጥ በሚገኙ ግብዓቶች ላይ ተመስርቶ ዲዛይኑን ማዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ | 6) The design consultant should prepare construction designs based on local materials. |
| 7) የግንባታ ግብዓቶች በአገር ውስጥ የማይገኙና ከውጪ አገር የሚመጡ ግብዓት ከሆኑ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ውሳኔ መሰረት የሚዘጋጅ ይሆናል፡፡ | 7) If construction materials are not available locally and are imported, they shall be prepared in accordance with the decision of the Ministry. |
| 8) የግንባታ የዲዛይኑ የቆረጣ ምልከታ ተወስዶ ዝርዝር ዲዛይኖችን፣ መለኪያዎችን እና የግብዓት ዝርዝሮችን በግልጽ ማስቀመጥ ይኖርበታል፡፡ | 8) The construction design section should be taken into account and put clearly detail the design parameters and inputs. |

7. **<u>የዲዛይን ዝግጅት ዝርዝር ተግባራት</u>**

አማካሪው ዲዛይን በሚያዘጋጅበት ወቅት የሚከተሉትን ዝርዝር ተግባራት ማከናወን ይኖርበታል፡-

1) የመስክ፣ የከርሰ-ምድርና የአፈር ፍተሻ/ምርመራ አሠሪው የመስክ፣ከርሰ-ምድርና አፈር ምርመራ (ፍተሻ) ሲከናወን ቢያንስ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡-

ሀ) የግንባታ ፕሮጀክቱ የሚያርፍበትን ሥፍራ በፕሮጀክቱ እቅድ እና ከፕሮጀክቱ ጋር ተዛማጅነት ባላቸው መስፈርቶች መሠረት ወካይ የከርሰ-ምድርና የአፈር ናሙና መውሰድ ፍተሻ/ምርመራ ማድረግ፤

ለ) የከርሰ-ምድርና አፈር ምርመራ ለማድረግ የተጠቀመውን የአፈር ምርመራ ዘዴ እና ተደራሽነቱን ያካተተ ዝርዝር መረጃ ማቅረብ፤

ሐ) የተገኘውን የከርሰ-ምድርና አፈር ምርመራ ውጤት መሰረት በማድረግ ለሚያዘጋጀው ዲዛይን እና ለግንባታ ቦታው ተገቢነት ያለው ሙያዊ አስተያየትና የተሸለ የዲዛይን አማራጭ በጽሁፍ ማቅረብ፤

2) **<u>የሥራ ዝርዝር</u>**

አግባብ ባለው መሥሪያ ቤት የተፈቀዱ ቴክኒካዊ የስራ ዝርዝሮች እና የመለኪያ ዘዴዎች መሰረት የሥራ ዝርዝሮች ሲዘጋጁ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማሟላት ይኖርባቸዋል፡-

ሀ) አማካሪው የሚያዘጋጀው የሥራ ዝርዝር ሰነድ መለኪያዎችን እና የይዘት መስፈርያዎችን መሠረት ያደረገና ያሟላ መሆን፣

7. **<u>Design preparation details</u>**

The consultant should perform the following detailed tasks in preparing the design:

1) Site፣ Groundwater and Soil Inspection The employer must at least verify the following when conducting a field, groundwater and soil inspection.

A) Carry out representative ground and soil sampling at the site of the construction project in accordance with the project plan and project related requirements

B) Provide detailed information on the groundwater exploration methods and accessibility used for groundwater and soil testing;

C) Provide relevant professional feedback and a better design option for the design and construction site based on the results of the subsoil survey

2) **<u>Specification</u>**

When preparing specification in accordance with the technical specifications and measurement methods approved by the relevant office, they must meet the following:

A) The specification document prepared by the consultant is based on and meets the criteria and content standards

ለ) ከዲዛይኑ በመነሳት ሊሰራ ለታሰበው ሥራ አስፈላጊውን የግብዓት ዓይነቶች ፣ይዘትና ጥራት በዝርዝር የሚገለጽ መሆን፤

ሐ) ዲዛይኑ የሚያካትታቸው የግንባታ ግብዓቶች ከውጪ ሀገር እንዲገዙ አስገዳጅ ሁኔታ ከሌለ በስተቀር በሃገር ውስጥ ገበያ ላይ ሊገኙ የሚችሉና ደረጃቸውን የጠበቁ መሆን፤

መ) የሃገር ውስጥም ሆነ የውጭ ግንባታ ግብአቶች የተረጋገጠ የጥራት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሊቀርብባቸው የሚችሉ መሆን፣

3) ***<u>ሥራ መጠን ትንተና እና ነጠላ ዋጋ ግመታ</u>***

ማንኛውም አማካሪ ድርጅት የሥራ መጠን ትንተና እና ነጠላ ዋጋ ግመታ ሲያዘጋጅ የሚከተሉትን ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅበታል፡-

1) ከዲዛይኑ በመነሳት ሊሰራ ለታሰበው ግንባታ የግንባታ ግብአት በዲዛይኑ ከተገለጸው ተጣጥሞ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

2) የሥራ መጠኑ ከዲዛይኑ ጋር በመጠንም ሆነ በይዘት የተጣጣመ ማድረግ፤

3) በአንድ ፕሮጀክት የነጠላ ዋጋ ትመና ውስጥ የተለያየ ትርፍና ልዩ ልዩ ህዳግ አለመጠቀም፣

4) የነጠላ ዋጋ ግመታ በሀገሪቱ ተቀባይነት ባለው የአሰራር ሥርዓት መሠረት የሚከተሉትን አካትቶ መከናወን አለበት፡-

ሀ) ለአንድ ሥራ የሚያስፈልግ የግንባታ ቁሳቁስ እና መጠን፣

B) Describe in detail the types, contents and quality of inputs required for the project to be constructed;

C) The construction materials included in the design shall be available in the domestic market and shall be standardized, unless otherwise required.

D) Ability to provide certified quality assurance of both domestic and foreign construction materials

**3) <u>Take-off and coast break down</u>**

Any consulting organization is required to implement the following when preparing a takeoff analysis and single price estimate:

1) Construction inputs for the intended construction should be prepared in accordance with the design.

2) Quantity of the work should be coinciding with the size and content of the design.

3) Not using different profits and margins in a single project price.

4) Single price estimation shall be carried out in accordance with the accepted procedures of the country፡-

A) Building materials and quantities required for a job

ለ) የሰው ሃይል እንደየሙያውና ድርሻው በስራው የሚቆይበት ጊዜ፣

ሐ) የግንባታ ማሽኖችና የእጅ መሳሪዎችን፣

መ) ለእያንዳንዱ የሥራ ዓይነት የሚያስፈልገው ቡድን በሰአት የሚሰራውን ሥራ መጠን በመጠቀም የዋጋ ግምት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

ሠ) የግንባታ እቃ ዋጋ፣የሰው ሃይል እና የሚያስፈልጉ ማሽኖችና የእጅ መሳሪዎችን ወቅታዊ የገበያ ዋጋ ከማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ ወይም ከሚመለከተው አካል በሚወጣ ዋጋ ዝርዝር መሰረት የሚዘጋጅ ይሆናል፡፡

## 8. <u>የኮንስትራክሽን ውል አስተዳደር ሥራዎች</u>

1) አሰሪው ወይም አማካሪው በውሉ መሠረት ተግባራቱ መፈጸማቸውን ተከታትሎ ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡
2) አማካሪው የተፈረሙ ውሎች መሠረት የግንባታ ሥራዎች በወቅቱ መጠናቀቁን ማረጋገጥ አለበት፡፡
3) ለማንኛውም የሕንጻ አማካሪ በውል አስተዳደር ለአገልግሎት የሚፈጸምለት ጥቅል ክፍያ ውስጥ በየጊዜው የሚፈጸመው በፕሮጀክቱ የግንባታ አፈጻጸም ደረጃ አንጻር በመቶኛ (በፐርሰንት) ተሰልቶ መሆን አለበት፡፡

## 9. <u>የግንባታ ሥራዎች ቁጥጥር</u>

የግንባታ ሥራዎች ቁጥጥር አማካሪ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማሟላት እና መተግበር አለበት፡፡

B) The duration of the workforce, depending on the profession and its role;

C) construction machinery and hand tools;

D) The team required for each type of work should estimate the cost based on the amount of work done per hour.

E) The current market price of construction materials, manpower and required machinery and equipment required shall be determined by the Central Statistics Agency or the relevant body.

## 8. **<u>Construction Contract Management</u>**

1) The employer or consultant must monitor and ensure that the activities are carried out in accordance with the contract.
2) Consultants must ensure that construction work is completed on time in accordance with signed contracts.
3) For any building consultant, the total cost of the contract for service management shall be calculated as a percentage based on the project.

## 9. **<u>Supervision of construction works</u>**

Construction Supervisor Consultant must meet and implement the following:-

A) Provide the contractor with a clear plan

| | |
|---|---|
| ሀ) የሥራ ተቋራጩ ግንባታ ስራውን ከመጀመሩ በፊት በግልጽ የተዘጋጀ የእቅድና የሥራ መርሃ-ግብር እንዲያቀርብ ማድረግ፣ | and work schedule before construction begins |
| ለ) አማካሪው ወደ ቁጥጥር ተግባር ከመግባቱ በፊት የቁጥጥር ማንዋል ማዘጋጀት፣ | B) Prepare a control manual before the consultant enters into a control operation |
| ሐ) አማካሪው ሥራ ተቋራጩ ወደ ተግባር ከመግባቱ በፊት እና በግንባታ ወቅት የደህንነትና የጥንቃቄ እርምጃዎችን ማሟላቱን ማረጋገጥ፣ | C) Ensure that the consultant meets safety and security precautions before and during construction |
| መ) አማካሪው የግንባታ ግብዓትና አቅርቦት ምንጮች ጥቅም ላይ ከመዋላቸው በፊት በሚወሰድ ወካይ ናሙና ፍተሻ ማድረግ፣ | D) The consultant shall Inspect sample taken from the source of the construction material before using it. |
| ሠ) አማካሪው የሥራ ተቋራጩ የግንባታ ደረጃ በየእለቱ በአካል በመገኘት ተገቢውን ክትትል በማድረግ በእለት መዝገብ ላይ እንዲይዝ ማድረግ፣ | E) The consultant shall follow up the construction status of the contractor on a daily basis. |
| ረ) እያንዳንዱ የግንባታ ደረጃ ሲጠናቀቅ ለተሠራው ሥራ ከሥራ ተቋራጩ ጋር በጋራ በመሆን ጥራቱን ተቀባይነት ባለው ፍተሻ ማረጋገጥ፣ | F) To ensure the quality of the work done at the completion of each stage of construction in collaboration with the contractor |
| ሰ) በተሰጠው የፀደቀ ዲዛይን፣ የሥራ ዝርዝር እና የውል ሰነድ መሠረት ሥራ ተቋራጩ ፕሮጀክቱን በተያዘለት ጊዜና ዋጋ እንዲሁም በተቀመጠው የጥራት ደረጃ እየገነባ ስለመሆኑ በመቆጣጠር፣ በመከታተል እና ከሥራ ተቋራጩ የተቀበለውን ጊዜያዊ ክፍያ ጥያቄ አረጋግጦ ለአሰሪው ማቅረብ፣ | G) Supervise that the contractor is constructing the project on time and at the specified price and quality level in accordance with the approved design, specification and contract document by Monitoring and verifying the temporary payment request received from the contractor to the employer |
| ቀ) የግንባታ ቁጥጥሩን /ሱፐርቪዥን/ ሲያከናውን አጠቃላይ ሥራውን በአግባቡ | H) Ensure that the construction supervision is based on a pre-designed checklist that allows it to supervise the overall operation. |

ለመቆጣጠር በሚያስችለው አስቀድሞ የተዘጋጀ ቼክ-ሊስት መሠረት መሆኑን ማረጋገጥ፣

በ) በግንባታ ቦታ ላይ የሚቀመጥ የስራ መዝገብ ያዘዛቸውን ስራዎች ዝርዝርና አጠቃላይ መረጃ፣ የየዕለቱን የሥራ አፈጻጸም በሳምንቱ መጨረሻ እንዲሁም የየሳምንቱን በወሩ መጨረሻ አጠቃሎ ለአሰሪው ሪፖርት ማቅረብ፤

ተ) በዚህ ንኡስ አንቀጽ ፍደል ተራ ‹በ› መሠረት የሚቀርብ ወርሃዊ ሪፖርት ቢያንስ በተግባር የተከናወኑ ሥራዎች የሚከተሉትን አካትቶ መቅረብ አለበት፤

(1) የተላለፉ ትዕዛዞች፣

(2) ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች፣

(3) የፕሮጀክቱን የፊዚካልና ፋይናንሺያል አፈጻጸም፣

(4) በፕሮጀክቱ የተሰማራ የሰው ኃይል በቁጥር፣በጾታ እና በሙያ ስብጥር፣

(5) በግንባታ ቦታ ላይ ያሉ የግንባታ ግብዓቶችና መሳሪያዎች ዝርዝር መግለጫ፣

(6) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከፊደል ተራ ሀ እስከ ተ የተዘረዘሩት እንደተጠበቀ ሆኖ የግንባታ ቁጥጥር አማካሪው ግንባታውን በተቀመጠለት የውል ጊዜ በዲዛይኑ መሰረት መገንባቱንና ለአገልግሎት ዝግጁ መሆኑን አረጋግጦ ለአሰሪው እንዲረከብ ማድረግ አለበት፡፡

I) Provide the employer with a detailed description of the book on the construction site, a summary of the daily performance over the weekend and a summary of each week's end of the month

J) A monthly report submitted in accordance with sub-paragraph (I) of this sub-article shall at least include the following activities

(1) Orders

(2) Problems encountered and solutions taken

(3) The physical and financial performance of the project

(4) The number of people engaged in the project in terms of number, gender and occupation

(5) A detailed description of the construction materials and equipment at the construction site

(6) Subject to the provisions of sub-paragraph A to J paragraphs of this subsection, the construction supervisor shall ensure that the construction is carried out in accordance with the design and is ready for use within the stipulated time.

**10. <u>የሙያ ሥነምግባር ግዴታዎች</u>**

እያንዳንዱ አማካሪ በሙያ ማሕበራት የተደነገጉ የሙያ ሥነ-ምግባር የማክበርና የማስከበር ግዴታ አለበት፡፡

**11. <u>ኮንትራት ስለማራዘም</u>**

አንድ አማካሪ ኮንትራት የማራዘም የውሳኔ ሐሳብ ሊያቀርብ የሚችለው በውሉ ሰነዶች ውስጥ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በሚከተሉት ጉዳዮች መሰረት አድርጎ መሆን አለበት፡-

1) የበጀት እጥረት በአሠሪው ተረጋግጦ ሲቀርብ፤
2) በአገር አቀፍ ደረጃ የግንባታ እቃ እጥረት መኖሩ ሲረጋገጥ፤
3) ግንባታው ያልተጠናቀቀው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑ ሲረጋገጥ፣
4) የክፍያ መዘግየት፣
5) የባለሙያ እጥረት መኖሩ በአሠሪው ሲረጋገጥ እና
6) በአሰሪው ፍላጎት በውል ያልተገለጹ ተጨማሪ ስራዎች ሲቀርቡ፡፡

**12. <u>የተመዘገቡ ባለሙያዎችን ቀጥሮ ስለማሰራት</u>**

1) ማንኛውም የተመዘገበ አማካሪ ከቅድመ ዲዛይን እስከ ግንባታ ማጠናቀቂያ ሥራ በተመዘገበና ደረጃውን በሚመጥን ባለሙያ ማሠራት አለበት፣
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚቀጠረው/በስራው የሚሳተፈው ባለሙያ የታደሰ ምስክር ወረቀት ያለው መሆን አለበት፡፡

**10. <u>Professional ethical obligations</u>**

Every counselor has a duty to respect and uphold professional ethics set by professional associations.

**11. <u>Extending the contract</u>**

A consultant may propose to extend the contract on the basis of the terms set out as follows with standings of the contract documents:

1) Budget shortfall confirmed by the employer
2) When there is a shortage of building materials nationwide
3) When determined that the construction was not completed due to overcrowding
4) payment delay and
5) When a professional shortage is confirmed by the employer
6) When additional work is not specified as specified by the employer

**12. <u>Recruitment of registered professionals</u>**

1) Any registered consultant shall employee registered and qualified professional from pre-design to construction completion.
2) The professional employed in accordance with sub-article 1 of this Article shall have a renewed certificate.

**ክፍል ሶስት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

13. **አስተዳደራዊ ቅጣት**

1) አማካሪው በዚህ መመሪያ ከአንቀጽ 5 እስከ 9 የተቀመጡትን ድንጋጌዎችን በመተላለፍ ጥፋት የፈጸመ እንደሆነ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አስተዳደራዊ ቅጣቶች ይወሰኑበታል፡-

ሀ) ጥፋቱ የመጀመሪያ ከሆነ እና ጉዳት ያላደረሰ መሆኑ ከተረጋገጠ የጽሁፍ ማሰጠንቀቂያ፡

ለ) ቀላል ጉዳት ያደረሰ ከሆነ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ ለአንድ ዓመት ይታገዳል፣

ሐ) ጉዳት እና ኪሳራው በቀላሉ ሊታረም የማይችል ከሆነ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ ለሁለት ዓመት ይታገዳል፣

መ) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ከፊደል ተራ ሀ እስከ ሐ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጥፋቱ ለሁለተኛ ጊዜ ከሆነ እና ጉዳት ማስከተሉ በሚመለከተው ተቋም ከተረጋገጠ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬቱ ለአራት አመት እንዲታገድ ይደረጋል፡፡

ሠ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ አማካሪው ሆን ብሎ ለራስ ጥቅም ወይንም ለሌሎች ጥቅም ለማስገኘት ብሎ በሥራው ላይ ብክነት እንዲፈጠር ማድረጉ ከተረጋገጠ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬቱን በመሰረዝ ለመድን ያስያዘው የዋስትና መጠን ለአሰሪው ማካካሻ ይሆናል

ረ) አማካሪው ለርክክብ ብቁ የሆኑና ግንባታቸው የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶችን ያለበቂ ምክንያት ርክክብ እንዲፈጸም ያላደረገ እንደሆነ

**Part Three**

**Various provisions**

13. **Administrative Punishment**

1) If the consultant commits an offense in violation of the provisions of Articles 5 to 9 of this directive, the administrative penalties listed below shall be determined.

A) Written notice if the fault is original and it is determined that it did not cause damage

B) In the event of minor damage, the certification will be suspended for one year

C) If the damage and loss cannot be easily corrected, the certificate of competency will be suspended for two years

D) Without prejudice to the provisions of sub-article 1 (A) up to (C) of this Article, if the offense is a second time and the damage is determined by the relevant institution, the certification certificate shall be suspended for four years.

E) Notwithstanding the provisions of sub-article 1 of this Article, if the consultant is found to have intentionally wasted his work for personal gain or for the benefit of others, the cancellation of the qualification certificate and the amount insured will be compensated.

F) The Certificate of Competence will be suspended for three years if the consultant fails to hand over the projects that are

| | |
|---|---|
| የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬቱ ለሶስት ዓመት ይታገዳል፡፡ | qualified for completion and completed without good reason. |
| (ሰ) በግንባታ ወቅት የደህንነት እና የጥንቃቄ እርምጃዎችን ሳያሟላ ተቋራጩ ወደ ሥራ መግባቱን ተመልክቶ በቸልተኝነት ያለፈ አማካሪ በንብረት እና በሰው ሕይወት እንዲሁም አካል ላይ ለሚደርሰው ጉዳት በተናጠል ወይም ከተቋራጩ ጋር ተጠያቂ ይሆናል፡፡ | G) A negligent consultant who observes the contractor entering into work without complying with safety and security measures during construction may be liable individually or jointly with the contractor for damage to property and human life and body. |
| (ሸ) አማካሪው የክፍያ ጥያቄ ቀርቦለት ለአሰሪው በተቀመጠው ጊዜ ገደብ መሰረት የክፍያ ጥያቄውን ሳያስተላልፍ ካዘገየ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬቱ ለአንድ ዓመት እንዲታገድ ይደረጋል፡፡ | H) If the consultant receives a payment request and delays the submission of the payment within the time limit set by the employer, the certification certificate shall be suspended for one year. |
| (ቀ) ማንኛውም የግንባታ አማካሪ በአንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 3 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የግንባታ ግብአት መጠን ከተዘጋጀው ዲዛይን ጋር በተጋነነ መልኩ ልዩነት ያለውን ካቀረበ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬቱ ለሶስት አመት እንዲታገድ ይደረጋል፡፡ | I) The construction certificate shall be suspended for a period of three years if any construction consultant exaggerates the amount of construction inputs that are contrary to the design in accordance with the provisions of sub-article 3 of Article 7. |
| ረ) ማንኛውም አማካሪ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬቱ የስረዛ ወይም የእግድ ቅጣት የተጣለበት እንደሆነ ውሳኔው በተላለፈ በ10 (አስር) የስራ ቀናት ውስጥ ቀርቦ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬቱን ለሰጠው አካል ተመላሽ ማድረግ አለበት፡፡ | J) Any consultant shall, within 10 (ten) working days of the decision, submit his / her certification to the issuing authority if the certificate of revocation is suspended or suspended. |
| ሸ) እግድ ወይም ስረዛ ያስተላለፈው ተቋም በደብዳቤ ለሚመለከተው አካል የሚያሳውቅ እና በተቋሙ ይፋዊ ድረ-ገጽ ላይ ያሳውቃል፡፡ | K) The institution that issued the suspension or cancellation shall inform the concerned party in writing and on its official website |

| | |
|---|---|
| 14. **<u>የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት</u>** | 14. **<u>Complaint system</u>** |
| 1) በዚህ መመሪያ አንቀፅ 11 መሰረት ቅጣት የተጣለበት ማንኛውም አማካሪ ፣ የተጣለበት እገዳ ወይም ስረዛ እንዲሻሻልለት ወይም እንዲነሳለት፤ እግዱን ያስተላለፈው አካል ተጠሪ ወደ ሆነበት የመንግስት አካል መታገዱን ወይም መሰረዙን ባወቀ በ15 ተከታታይ ሥራ ቀናት ውስጥ አስተዳደራዊ አቤቱታውን ማቅረብ ይችላል፡፡ | 1) Any consultant who has been punished in accordance with Article 11 of this directive shall be entitled to amend or revoke the suspension or cancellation. The issuing body may file an administrative appeal within 15 consecutive working days after it is notified that it has been suspended or canceled. |
| 2) አቤቱታ የቀረበለት አካልም አቤቱታው በደረሰው በ10 ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ መልስ መስጠት አለበት፣ | 2) The respondent must respond within 10 working days of receiving the complaint. |
| 3) አቤቱታ አቅራቢው በተሰጠው ምላሽ ያልረካ እንደሆነ ምላሹ በደረሰው በ10 ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ለሚኒስቴሩ ማቅረብ ይችላል፤ ለሚኒስቴሩ የሚያቀርበው አስተዳደራዊ አቤቱታም የመጨረሻ ይሆናል፡፡ | 3) If the complainant is dissatisfied with the response, he may file a complaint with the Ministry within 10 consecutive working days of receiving the response; His administrative appeal to the Ministry will be final. |
| 15. **<u>የማማከር ሥራ ከተቋረጠ ወይም ከተጠናቀቀ በኋላ የሚታወቁ ጥፋቶች</u>** | 15. **<u>Errors identified after termination or completion of counseling</u>** |
| ማንኛውም አማካሪ የማማከር ሥራውን ካቆመበት ወይም ካጠናቀቀበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 10 (አስር) አመት ድረስ ከሰራቸው የዲዛይንና የማማከር ሥራዎች ጋር ተያይዞ በፕሮጀክቱ ላይ የሚከሰቱ ችግሮች በግንባታ ወቅት እንደተከሰቱ ተቆጥረው እንደ ጥፋቱ ዓይነትና ክብደት ይጠየቃል፡፡ | Problems with the project related to the design and consulting work performed by any consultant for 10 years from the date of termination or completion of the consulting work shall be considered as the nature and severity of the damage. |
| 16. **<u>የሌሎች ህጎች ተፈጻሚነት</u>** | 16. **<u>Enforcement of other laws</u>** |
| የዚህ መመሪያ ስራ ላይ መዋል የወንጀል እና የፍትሐ-ብሔር ሕግ ድንጋጌዎች እንዲሁም ሌሎች የኢትዮጵያ ህጎች ተፈጻሚነት ሊያስቀር አይችልም፡፡ | The application of this directive does not preclude the application of criminal and civil law provisions as well as other laws of the Ethiopia. |

| | |
|---|---|
| 17. <u>*መመሪያውን ስለማሻሻል*</u> | **17. <u>Improving the directive</u>** |
| ይህንን መመሪያ ማሻሻል ሲያስፈልግ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡ | This directive may be revised by the Ministry when required. |
| 18. <u>*መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ*</u> | **18. <u>Time of validation of the directive</u>** |
| ይህ መመሪያ ከመጋቢት 21 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ነው፡፡ | This directive is effective from the date of March 30/ 2022. |
| ወ/ሮ ጫልቱ ሳኒ<br>የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር<br>ሚኒስትር | Mrs. Chaltu Sani<br>Minister of Ministry of Urban and Infrastructure |